የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፴፰
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 38
ADDIS ABABA, 10th July, 2026

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፪/፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቬትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ ወይም ኦፊሻል/ አገልግሎት ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ…………………………………………ገጽ ፲፱ሺ፯፻፹፪

## Content

Proclamation No. 1422/2026

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Socialist Republic of Vietnam on Waiver of Visa Requirement for Holders of Diplomatic or official /Service Passports Ratification Proclamation.................
..................................................…....Page 19782

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፪/፪ሺ፲፰

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በቬትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ ወይም ኦፊሻል / የአገልግሎት ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተደረገውን ስምምነት ለማጸደቅ የወጣ  አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቬትናም ሶሻሊሸት ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ ወይም ኦፊሻል/ አገልግሎት ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት እ.ኤ.አ ኦገስት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ ስምምነት የተፈረመ በመሆኑ፤

### PROCLAMATION No. 1422/2026

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE SOCIALIST REPUBLIC OF VIETNAM ON WAIVER OF VISA REQUIREMENTS FOR HOLDERS OF DIPLOMATIC OR OFFICIAL /SERVICE PASSPORTS**

**WHEREAS**, the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Socialist Republic of Vietnam on waiver of Visa Requirement for Holders of Diplomatic or official /Service Passports was signed in Addis Ababa on the 23rd day of August 2018;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ባካሄደው ፳፫ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቬትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ ወይም ኦፊሻል/ አገልግሎት ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፪/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ሥምምነቱ ስለ መጽደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቬትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ ወይም ኦፊሻል/ አገልግሎት ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት እ.ኤ.አ ኦገስት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ጸድቋል።

**፫. <u>አስፈፃሚ አካል</u>**

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይህንን ስምምነት የማስፈጸም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**WHEREAS**, the House of Peoples Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified this agreement at its 23rd Regular Session held on 4th day of June, 2026;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Socialist Republic of Vietnam on Waiver of Visa Requirement for Holders of Diplomatic or official /Service Passports Ratification Proclamation No. 1422/2026".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Socialist Republic of Vietnam on Visa Exemption for Holders of Diplomatic or official / Service Passports signed in Addis Ababa, on 23 August 2018 is hereby ratified.

**3. <u>Implementing Organ</u>**

The Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia in collaboration with the relevant authorities is hereby empowered to implement this Agreement.

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 10th day of July, 2026**

**TAYE ATSKESELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**